# አዳም ስሚዝ ይህንን ቢያይ ኑሮ በጣም ይደነግጥ ነበር !

ከፈቃዱ በቀለ

***ቁጥጥር አልባ የሆነውን ካፒታሊዝም የሚያስፋፉ የኢኮኖሚ ምሁራን ዓለምን እንደዚህ ዐይነት ቀውስ ውስጥ የከተቷት የኢኮኖሚ መሠረተ-ሃሳቦችን በተሳሳተ መልክ ስለተረዱት ነው። አዳም ስሚዝ ስለገበያ ኢኮኖሚ ሲጽፍ በፍጹም ጭፍን የሆነ አመለካከትን አልሰበከም። ሊበራሉ ስሚዝ፣ እሴትን(value) እንዲሁም ደግሞ የኢንስቲቱሽኖችን በህግ መገዛት አስፈላጊነት አጥበቆ በማንሳት አስተምሯል።***

Professor Amartya Sen

የኢኮኖሚና የፍልስፍና መምህር

ሌኒን ከ90 ዐመት በፊት በዚያን ጊዜ ስለተከሰተው የኢኮኖሚ ቀውስና ስለካፒታሊዝም የወደፊት ዕድል አንድ ቁም ነገር ተናግሮ ነበር። በሱ አገላለጽ ካፒታሊዝም ያለቀለት ነውና ስለዚህ እንዘንለት ማለት አንችልም፤ ካፒታሊዝም ከዚህ ቀውስ ሊወጣ አይችልም ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ትልቅ ስህተት ነው ብሎ ተናግሮ ነበር። ሌኒን በሌሎች አነጋገሩ ሁሉ ሲሳሳት እዚህ ላይ ግን በፍጹም አልተሳሳተም። በ1920ዎቹና በ1930ዎቹ የኢኮኖሚ ቀውስ ስር እየሰደደ ቢሄድም፣ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ

ግን የገበያ ኢኮኖሚ በታሪክ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ፍጥነትና ውስጠ-ኃይል ሊስፋፋ ችሏል። ባለፉት 60 ዐመታት የታየው የኢኮኖሚ ዕድገትና ዓለምን ማዳረስ የካፒታሊዝምን ውስጠ-ኃይል ያረጋግጣል።

ለጊዜውም ቢሆን እንደዚህ ዐይነቱን ዕምርታ ያስመሰከረው ካፒታሊዝም ሊገታ ችሏል። ያበቃለት ይመስላል። ዛሬ አፍጦ አግጦ የሚታየው ዓለም አቀፋዊ የኢኮኖሚቀውስ የጀመረው በአሜሪካን ሲሆን፣ብዞዎቻችንን አሳስቧል። የካፒታሊስት አገሮች መንግስታት በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠር የህዝብ ገንዘብ በኢኮኖሚው ውስጥ ቢያፈሱምቀውሱ ግን ሊገታ አልቻለም።

አሁን የሚቀርበው ጥያቄ ካፒታሊዝም ያለቀለት ነው ብሎ መደምደም ሳይሆን፣ ወደ ፊት ካፒታሊዝምን እንዴት በአዲስ መልክ ማደራጀት ይቻላል ብሎ ማውጣትና ማውረድ ነው። በዚህ ዐይነት ሊቀጥል ይችላል ወይ? ወይስ ውስጣዊ ይዘቱ መቀየር አለበት ? ለጊዜው ችግሩ ሊፈታ የማይችል ቢመስልም አንድ ቀን ግን ከቀውሱ መላቀቅ ይቻላል። ማንኛውም ስርዓት የካፒታሊዝም ዐይነት ስርዓት አይደለም !

ሁኔታው እንደዚህ አስቸጋሪ ከሆነ የሚቀረው ነገር የወደፊቱን የኢኮኖሚ ስርዓት ውስጣዊ ይዘት የመፈለጉ ጉዳይ ነው። በእርግጥስ የካፒታሊዝምን ባንዲራ ይዞ ማውለብለብ የሚያስችል አዲስ ዐይነት የካፒታሊስት ስርዓት ያስፈልጋል ወይ? ወይም አዲስ ዐይነት ያልተወሳሰበና አንድ ወጥ ያልሆነ፣ በብዙ እግሮች መቆም የሚችልና በኢንስቲቱሽኖች ተደግፎ በአርቆ አስተዋይነት ሊመራ የሚችል? አዲስ ዐይነት ካፒታሊዝም

እንፈልግ ወይስ ደግሞ በካፒታሊዝም መሰረተ-ሃሳብ ላይ ያልተመረኮዘ "አዲስ ዓለም" ለመመስረት እንሯሯጥ?ከዚህ አስቸጋሪ ጥያቄ ፊት እኛ ብቻ አይደለንም

የቆምነው። እንደማምነው ከሆነ፣ አዳም ስሚዝ በ18ኛው ክፍለ-ዘመን ታዋቂውን ሰለገበያ ኢኮኖሚ የሚያትተውን መጽሀፉን ሲጽፍ፣ ይህ ዐይነቱ አስቸጋሪ ጥያቄ ከፊቱ ተደቅኖ ነበር።

እስከማውቀው ድረስ፣አዳም ስሚዝ „ካፒታሊዝም" የሚለውን ፅንሰ-ሃሳብ በፍጹም አልተጠቀመም። በተጨማሪም ቀስ በቀስ እያለ የበላይነትን እየተቀዳጀ ስለሚወጣው ካፒታሊዝም ከመጽሀፉ ውስጥ ፈልጎ ማግኘት አይቻልም። አዳም ስሚዝ "የአገሮች ሀብት" (The Wealth of Nations) በሚለው መጽሀፉ ውስጥ አጥብቆ የሚያነሳው ነገር አለ። ይኸውም አጠቃላይ የሆነ ስነ-ምግባርን መቀበልና ከዚህም ጋር ሊሄዱ የሚችሉ ኢንስቲቱሽኖች መኖር እንዳለባቸው ያሳስባል። በተለይም ከ250 ዐመት በፊት ስነ-ምግባርን
አስመልክቶ ስለጻፈውና „የስነ-ምግባራዊ ስሜት" (The Theory of Moral Sentiments) በሚለው
መጽሀፉ ውስጥ ከትርፍ ወይም የራስን ጥቅም ከማሳደድ ጋር ያልተያያዘ ህብረተሰብአዊ ስነ-ምግባር የቱን ያህል ለአንድ ህብረተሰብ ዘላቂነትና ተቻችሎ መኖር አስፈላጊ እንደሆነ በሰፊው ጽፏል።ከማንኛውም በላይ ይላል ስሚዝ፣ በማንኛውም ድርጊት ጊዜ እያንዳንዱ ግለሰብ የሚወስዳቸው እርምጃዎች ከፍተኛ እሴትን ያዘሉ መሆን አለባቸው።
በመቀጠልም፣ ሰብአዊነት፣ ቸርነት፣ ለእኩለነት መታገልና ህብረተሰብአዊ ስሜትን ከሰውነት ጋር ማዋሃድ የማንኛውም ግለሰብ መመሪያዎች መሆን እንዳለባቸው ያሳስባል። በነዚህ መሰረተ-ሃሳቦች ብቻ መመራት ሲቻል በእርግጥም አንድ ህብረተሰብ ከሞላ ጎደል ጤናማ ሊሆን ይችላል ብሎ ያስተምራል። ለመሆኑ ካፒታሊዝም ማለት ምን ማለት ነው? ተቀባይነት ባለው ትርጉም፣ ካፒታሊዝም ማለት የግዴታ በገበያ ላይ በሚሽከርከር የዕቃ-ገንዘብ ልውውጥ ላይ የተመሰረተ ነው። በተጨማሪም፣ ለትርፍ መስራትና የግል ሀብት መኖር የካፒታሊዝምን ምንነት ይገልጻሉ። ይህ ከሆነ በአሜሪካና በአውሮፓ የሚገኘው ስርዓት በእርግጥስ ካፒታሊስታዊ ነው?

ሁሉም የአውሮፓ አገሮች፣ አሜሪካ፣ ካናዳ፣ጃፓን፣ሲንጋፖር፣ደቡብ ኮርያ፣ አውስታራሊያና እንዲሁም አንዳንድ አገሮች ከገበያ ውጭ የሚደረግ ልውውጥ ሲያደርጉና ጥቅም ሲያገኙ እናያለን። የስራ-አጥ አበል፣ በመንግስት የተደገፈ የጡረታ አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችና እንዲሁም ደግሞ በመንግስት የሚደገፍ የትምህርትና የጤና ተቋማት ከስርዓቱ ጋር አብረው ሲሄዱ እናያለን። ሁሉም የካፒታሊት አገሮች ወይም ደግሞ ከሞላ ጎደል በዚህ ስርዓት ውስጥ የሚካተቱ ሁሉ ትርፍን ማካበት በሚለው መርህ ላይ ብቻ
አትኩረው አያውቁም። ይህንን ብቻ መሰረት አድርገው ሲንቀሳቀሱ አልታየም። አብዛኛውን ጊዜ ብዙዎች ምሁራን አዳም ስሚዝ ርቃኑን የሚሄድና ትርፍን ማካበት መሰረት ያደረገ የገበያ ኢኮኖሚ እንደጻፈ ነው የሚረዱትና
የሚያስተምሩት።በማንኛውም ቦታ ስሚዝ ይህንን ዐይነቱን የተሳሳተ አመለካከት አልጻፈም።
አላስተማረምም። ስሚዝ በተወሰነ መልክ የጻፈው፣ ለምን ሰዎች በንግድ ዓለም ውስጥ መሳተፍ እንዳለባቸውና ምንስ እንደሚያስገድዳቸው ነው። ይህንን መሰረታዊ አስተሳሰብ ወስዶ ለማንኛውም ህብረተሰብአዊ ግኑኝነትና ኑሮ መመሪያ ማድረግና

የጠቅላላውም የሰው ልጅ አስተሳሰብና ኢንስቲቱሽኖች በዚህ እንዲሽከረከሩ ማድረግና መስበክ ትልቅ ወንጀል ነው። የስሚዝ ደቀ-መዙሙር ነን የሚሉ የኢኮኖሚ ምሁራን የሚሰሩት ወንጀል የስሚዝን ትምህርት በማጣመም ነው።

ሰዎች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ በንግድ ዓለም ውስጥ ይሳተፋሉ። በየጊዜው እየተደጋገመ የሚነገር አንድ ነገር አለ። ዳቦ ጋጋሪዎች፣ ቢራ ጠማቂዎች፣ ስጋ ሻጮችና ተጠቃሚዎች ለምን እንደሚነግዱና እንደሚለዋወጡ ይጻፋል። ይሁንና ገበያ ካለምንም መረበሽ ለመንቀሳቀስ እንዲችል ከመሸጥና ከመግዛት ባሻገር ሌሎች መሰረተ-ሃሳቦችም እንዳሉ መገንዘብ ያስፈልጋል። ይኸውም መተማመንና ነገሮችን ጠጋ ብሎ መመልከትና
እንዲሁም በሚያደርጉት ስራ ሁሉ እርግጠኛ መሆንን ለገበያ ኢኮኖሚ መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው። ስሚዝ በመቀጠልም እንዲህ ይላል። የአንድ አገር ህዝብ ባንኮች ውስጥ በሚሰሩ ሰራተኞች አነጋገር ረጋ ማለትና ማሳመን ሲመሰጥና ምክራቸውንም ሲቀበል በተለያየ መልክ ያስቀመጠውን ገንዘብ አንድ ቀን መልሶ አገኛለሁ ብሎ በማመን ነው። ይህም ገንዘብ ልክ እንደ ወርቅና ብር ተመሳሳይ ዋጋ ይኖረዋል ብሎ በመገምት ነው። ያስቀመጠው ገንዘብ እንዳለ ሲመለስለት ዕምነቱ ይጠነክራል።

አዳም ስሚዝ እንደዚህ ዐይነቱ ዕምነት ለምን ሁል ጊዜ ለመኖር እንደማይችል ገልጿል። የዳቦ ጋጋሪዎችን፣የስጋ ነጋዴዎችንና ይህንን የመሳሰሉትን አራማጆች-የነጻ ንግድ-የአሁኑን የኢኮኖሚ ቀውስ በደንብ የተረዱ አይመስልም። ከቀውሱ ለመውጣትም አስቸጋሪ እንደሆነ በደንብ የተገነዘቡ አይመስልም። አዳም ስሚዝ ይህንን ስራቸውን ቢመለከት ለምን ይህ ሁኔታ መፈጠር እንደቻለ በፍጹም አይደንቀውም።
በእርግጥ ላለመተማመንና በፍርሃት ለመዋጥ በቂ ምክንያት አለ። በአለፉት ዐመታት ግዴታቸውን የጣሱትንና አለመተማመን እንዲፈጠር ያደረጉትን መከታተል በጣም አስቸጋሪ ሆኗል። ለዚህ ሁሉ አለመተማመንና ቀውስ የምንከሰውና የምናመሰግነው ሁለተኛ ገበያ(Secondary Market) እየተባለ በሚጠራው ላይ የሚሽከረከረው የአክሲዮን ወረቀት፣ ዴሪቫቲብና ልዩ ልዩ የፋይናንስ ምርቶች(Financial Products) የሚሸጡትንና የሚያሽከረክሩትን ነው። ይህ ዐይነቱ የቁማር ጨዋታ ይካሄድ የነበረው ጥቂት አገሮች
ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የውጭ ንግድ ሚዛናቸው በጣም ጥሩ ውጤት ባመጣበት ጊዜና ብዙ የውጭ ገንዘብም እየተከማቸ በመጣበት ወቅት ነው። ይህም የተትረፈረፈ ገንዘብ ለተጨባጭ ኢኮኖሚው እንዲያገለግል በብድር መልክ ሊሰጥ የሚችል ነበር። ይሁንና ግን በዚህ በተትረፈረፈ ገንዘብ በመሳከር፣ ባንኮች፣ የክሬዲት ኢንስቲቱሽኖችና ቁማር ተጫዋቾች ገንዘቡን ብዙ ዋስትና ማስያዝ ለማይችሉ ማበደርና ቤት እንዲገዙ አደረጉ። በዚህ መልክ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦችን በማታለልና እንደገና ደግሞ ዕዳውን ለሌላ በመሸጥ ቀውሱ ሌሎችንም እንዲያዳርስ አደረጉ።

ባለፉት ዐመታት የፋይናንስ ገበያውን መቆጣጠር ከምንግዜውም የበለጠ አስፈላጊ እየሆነ መጥቷል። ይሁንና ከፍተኛ ቁጥጥር በሚያስፈልግበት ሰዓት በብዙ የኢንዱስትሪ አገሮች፣ በተለይም ደግሞ በአሜሪካ ገበያ ራሱን በራሱ መቆጣጠር

ይችላል እየተባለ በመሰበኩና ቁጥጥሩ እየላላ በመምጣቱ እንደዚህ ዐይነት ቀውስ ሊፈጠር በቃ። እንደዚህ ዐይነቱ የኢንስቲቱሽኖች መዳከም፣ የቁጥጥር መላላት ለብዙዎች የበለጠ በቁማር ጨዋታው እንዲገፉበትና ሌሎችም በዚህ ውስጥ ገብተው ተቋራጭ እንዲሆኑ አመቻችላቸው። ስሚዝ እንደነዚህ ዐይነት አልጠግብ ባዮችን ዕምነት ሊጣልባቸው የማይችሉ ነጋዴዎች ብሎ ይጠራቸዋል። ይህ ዐይነቱ አባባል በተለይም ሰብ-ፕራይም የተባለው የቁማር ጨዋታ ላይ የተሳተፉትንና ብዙዎችን ያታለሉትን ይመለከታል።ይህም ማጭበርበር እንደጥበብ ስለተወሰደና ከዕውነተኛው የገበያ ኢኮኖሚ ጋር ስለተሰበከ ብዙዎቹ ወደ ማጭበርበር አመሩ። የአሜሪካ መንግስት ለዚህ ዐይነቱ ከፍተኛ ቀውስ ከተጠያቂነት ሊያልፍ የሚችል አይደለም። ይህ ዐይነቱ የገበያ ኢኮኖሚ ሰበካ ግን ከአዳም ስሚዙ የገበያ ኢኮኖሚ በብዙ እጅ ይለያል። ይሁንና ግን በዚህ የማጭበርበር ድርጊታቸውና የውሸት ሰበካም ብዙዎች እንደተደናገጡ ማንበብ ይቻላል።

## ዓለምን እንዴት በሚያስተማምን መልክ ማደራጀት ይቻላል?

ስሚዝ የገበያን ኢኮኖሚ ስፈላጊነትና ሚና ቢጽፍና ጠበቃ ቢሆንም፣ በሌላ ወገን ግን እዚያው በዚያው በጥሩ መልክ በሚንቀሳቀስ የገበያ ኢኮኖሚ ውስጥ ድህነት፣ መጻፍና ማንበብ _አለመቻል እንደሚስፋፉና ሌሎችም ለሰው ልጅ አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ ነገሮች ሊታጡ እንደሚችሉ ተገንዝቧል። ሰሚዝ የፈለገው ግለሰቦች በራሳቸው ጥረት እንዲንቀሳቀሱና በዚያውም መጠን ብዙ እንስቲቱሽኖች ተፈጥረው ህብረተሰቡን እንዲቆጣጠሩ ሲያሳስብ በምንም ዐይነት ግን አንድ ወጥ ስርዓትና ለትርፍ ብቻ መሮጥን በፍጹም አላስተማረም። ስሚዝ የገበያ ኢኮኖሚ ተግባራዊ ሊሆን በማይችልባቸው መስኮች፣ እንደ ጤንነትና የትምህርት መስክን የመሳሰሉትንና ድህነትን ማስወገድ የመንግስት ሚና እንደሆኑ አጥብቆ አሳስቧል። ኢንስቲቱሽኖች ሁሉ ከችግሮች ጋር እንዲጣጣሙና ችግሮችን ሊፈቱ በሚችሉበት ሁኔታ መዘጋጀት እንዳለባቸው አስተምሯል። ስለሆነም በምንም ዐይነት ሁሉም ነገር ለገበያው መለቀቅ እንደሌለበትና በገበያ „ፍልስፍናም“ ሊፈታ እንደሚችል ተደርጎ መወሰድ እንደሌለበት አመልክቷል።

በእኔ ዕምነት የዛሬው ቀውስ ወደ አዲስ ካፒታሊዝም የሚመራ አይደለም። ወይም ደግሞ በዚያ ላይ መረባረብ የለብንም። ከዚህ ይልቅ ግን ስለ ገበያ ኢኮኖሚ ምንነትና ገደብ ካለምንም ፍርሃት መከራከርና መወያየት አለብን። በተለይም የተለያዩ ኢንስቲቱሽኖች እንዴት እንደሚሰሩና ስራቸውን እንደሚያስተባብሩ ጠጋ ብሎ መመርመርና ማደራጀት ያስፈልጋል። ከዚህ በላይ ደግሞ፣ የተለያዩ ኢንስቲቱሽኖች የገበያውም ጭምር ከመንግስት ጋር በመሆን ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዳለባቸውና ህብረተሰቦቻቸውን በምን መልክ ማደራጀት እንደሚችሉ ማጥናትና መመርመር አለባቸው።∞

*በፕሮፌሰር አማርታያ ሴን የተጻፈ የኖቬል ዋጋ ተሸላሚ ናቸው ጽሁፉ በ19.03.09 ከእንግሊዘኛ ወደ*
*ወደ ጀርመንኛ ተተርጉሞ በፋይናንሺ ያል ታይምስ ላይ የወጣ ነው።*
**ተርጓሚው ፈቃዱ በቀለ**

## የተርጓሚው አስተያየት

በተለይም ካለፈው መስከረም ወር ጀምሮ ስር እየሰደደ የመጣው የኢኮኖሚ ቀውስ የሚያመለክተው ፍራንሲስ ፉኩያማ ለማሳመን እንደሞከረው የታሪክ መጨረሻ ላይ እንዳልደረስን ነው። በካፒታሊዝም ታሪክ ውስጥ ከሶስትና ከአራት በላይ የሆኑ ተደጋጋሚ ቀውሶች ተከስተዋል። በርግጥም ካፒታሊዝም ያለፉትን ቀውሶች ሁሉ ተቋቁሞ በአዲስ መልክ እየተደራጀ እዚህ ደረጃ ላይ ደርሷል። ባለፉት ስድሳ ዐመታት ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ምጥቀትም ታይቷል። የዛሬውን ቀውስ ዐይነተኛ የሚደርገው ግን ብዙ አገሮች በዓለም
አቀፍ ገበያ ላይ መሳተፋቸውና በየጊዜው ተመሳሳይ ምርት እያመረቱ መምጣታቸውና ወድድሩ መጦፉ ነው። በዚህም ምክንያት የዓለም ገበያ ከሚችለው በላይ የተትረፈረፈ ምርትን ለማሽከርከር የማይችልበት ሁኔታ እየተፈጠረ መጥቷል። በዚህ ላይ ትራዲሽናል የሆኑ የኢንዱስትሪ አገሮች በአዲስ በሚመጡ አምራች አገሮች ስለሚጠቁ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሀብት ሽግሽግና አለመመጣጠን እየተፈጠረ ነው። በተለይም እንደ አሜሪካ ያለው አገር የዓለም አቀፍን ሀብት በከፍተኛ ደረጃ በመጋራትና ወደ ውስጥ ደግሞ የራሱን
የማምረት ኃይል በማናጋት ለቀውሱ ዋና ምክንያት ሆኗል።

ፕሮፌሰር አማርታያ እንዳረጋገጡት፣ የገበያ ኢኮኖሚ ወደ መፈንጫነት በመለወጡ የብዙ ስዎችን አስተሳሰብ
መቀየሩ ብቻ ሳይሆን፣ ወደ ፊት ችግሩን በቀላሉ ለመፍታት የማይቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ የንግድ ልውውጥ አስፈላጊ የሆነውን ያህል፣ በየአገሮች ደግሞ መንግስታት ህብረተሰቦቻቸውን በፈለጉት መልክ ማደራጀትና ከቀወስ ነጻ እንዲሆን ማድረግ ታሪካዊና ህጋዊ ግዴታቸው ነው። የገበያ ኢኮኖሚ ለጥቂት ፈንጪዎች ዝም ብሎ የሚተው ነገር አይደለም። ማንኛውም ነገር ህግና ስርዓትን ተከትሎ መሄድ አለበት። ጥቂቶችን የሚያደልብ፣ አብዛኛውን ደግሞ ወደ ድህነት የሚገፈትርና የሚደቁስ የየህብረተሰቦች መመሪያ መሆን በፍጹም የለበትም።

ወደ አገራችን ስንመጣ ይህ ዐይነቱ የገበያ ኢኮኖሚ በተሳሳተ መልክ ስለተወሰደና ተግባራዊ ስለሆነ ህብረተሰባችን ፈሩን እንዲያጣ ሆኗል። ባለፉት አስራስምንት ዐመታት ጥቂቶች ሲደልቡ፣ ከዘጠና በመቶ በላይ የሚሆን ህዝባችን ወደ ድህነት ዓለም ተገፍትሮ ግራ ተጋብቶ እንዲኖር ተደርጓል። የሀብት በጥቂት ሰዎች እጅ መከማቸት፣ የከተማዎች ካለ ዕቅድ መሰራት፣ የአካባቢ መቆሸሽና የውሃ መመረዝ፣ ዶላር ለመቃረም ሲባል መሬታችን ለውጭ ከበርቴዎች መሸጥና አዲስ ዐይነት የህብረተሰብ ኃይል መፍጠር
የዚህ የተወላገደ የገበያ ኢኮኖሚ ዐይነተኛ ገጽታ ሆነዋል። አገራችን ዛሬ በቀጥታ ወደ እጅ አዙር የቅኝ አገዛዝ ስር ወድቃለች ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል።

ሰሞኑን በድህረ-ገጾች ላይ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ዕድገት አስመልክቶ ጥያቄዎች እየተነሱና እያከራከሩ ነው። የጥያቄውን አነሳስም ሆነ አስተያየት ለተመለከተ በኛ በኩል አሁንም ቢሆን የኢኮኖሚ ዕድገትን በሚመለከት የተዛባ አመለካከት እንዳለ መረዳት ይቻላል። ይህ የኛ የኢትዮጵያውያኖች ችግር ብቻ አይደለም። ሌሎች የሶስተኛው ዓለም አገሮችም ያለባቸው ችግር ነው። እስከማውቀው ድረስ ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት የተጻፉት

የዩኒቨርሲቲ መማሪያ መጽሀፎች በሙሉ ከኒዎ-ሊበራል አንጻር ነው። ሌሎች ይህንን የሚቃወሙና ሰለ ሰፊው ህዝብ ተሳትፎ አስፈላጊነትና ስለ መሰረታዊ ነገሮች(Basic Needs) መሟላት የሚያትቱ ግሩም ግሩም መጽሀፎች ታትመው በየመጽሀፍት ቤቱ አሉ። ይሁንና አብዛኛዎች የሶስተኛው ዓለም አገሮች መንግስታት፣ በተለይም ደግሞ የአፍሪቃ መንግስታት የእነ ዓለም ባንክንና የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትን (IMF) ምክር በመቀበልና ተግባራዊ በማድረግ በችግር ላይ ችግር በመፍጠር ሊወጡ የማይችሉት ማጥ ውስጥ ገብተው እዚያው በዚያ ሲንደፋደፉ ይታያል። መንግስታት ይህን ዐይነቱን አገር አፍራሽና ህብረተሰብአዊ ሀብት ሊፈጥር የማይችል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለምን በየጊዜው ይቀበላሉ ? ማንስ
ያስገድዳቸዋል ?

በእኔ ዕምነት፣ 1ኛ) አብዛኛዎቹ የአፍሪቃ መንግስታትና ኤሊቶች ህብረተሰበአዊና የታሪክ ኃላፊነት አይሰማቸውም። 2ኛ) ከየህብረተሰቡ ጋር የተቆላለፉ ምሁራዊ እንቅስቃሴዎች በፍጹም የሉም። ምሁሩና ሰፊው ህዝብ በሁለት በተለያየ ዓለም ውስጥ ነው የሚኖሩት። አንድ አፍሪቃዊ ከተማረ በኋላ በህዝቡ ትከሻ ላይ ቅጥጥ ማለት ይፈልጋል። ስለሆነም በሌሎች የአፍሪቃ የአገሮችም ሆነ በአገራችንም ውስጥ ሁለት ክስተቶች እየታዩ ነው። በአንድ በኩል የኤሊት ዘረኝነት፣በሌላ አነጋገር ህዝቡን መናቅና ለህዝቡ ደንታ
አለማሳየት፣ በሌላ ወገን ደግሞ ለአውሮፓና ለአሜሪካ ኤሊቶች ተገዢ መሆን። በዚህም ምክንያት የተትረፈረፈ ሀብት እያለና ይህንንም ባለው ቴክኖሎጂ መጠቀም ሲቻል ማንም እየመጣ እንዲዘርፈው ይደረጋል። ከሴራሊዮን እስከ ላይቤሪያ፣ ከናይጄሪያን እስከ ኮንጎ እንዲሁም ኢትዮጵያን ጨምሮ ያለው ችግር የየመንግስታቱ የአውሮፓና የአሜሪካ አሽከር መሆን ነው። በዚህም ምክንያት በአፍሪቃ ውስጥ ስለኢኮኖሚ ዕድገት ሳይሆን ማውራት የሚቻለው ስለሀብት ዘረፋ ነው።

እኛ ኢትዮጵያውያኖች ስለ አኮኖሚ ዕድገት ከማውራታችን በፊት ስለሰው ልጅ ምንነትና ሚና መመርመርና መወያየት ያለብን ይመስለኛል። ሰው ወይም የሰው ልጅ የሚለው ጽንሰ-ሃሳብ በጭንቅላታችን ውስጥ እስካለተቀረጸ ድረስ ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት በፍጹም ማውራት አንችልም። በኛ አገር ያለው መናናቅና ዘረኝነት መረን የለቀቀ ነው። በዚያ ላይ ስለስራ ያለን ትርጉም የተዛባ ነው። አንድ አገር ካለስራ የሚያድግ
የሚመስለን ጥቂቶች አይደለንም። አዳም ስሚዝም ሆነ ማርክስ እንዲሁም ደግሞ ከነሱ የቀደሙ የኢኮኖሚና የፍልስፍና ምሁራን ዋናው ሀብት ፈጣሪ ስራ እንደ ሆነ ነው የሚያስተምሩት። Only human labour can create value የሰው ጉልበትና የተፈጥሮ ሀብት አንድ ላይ ሆነው ህብረተሰብአዊ ሀብትን(National Wealth) ይፈጥራሉ። ይህ የፖለቲካ ኢኮኖሚ መሰረተ-ሃሳብ ነው። በእኛ አገርና በሌሎችም አፍሪቃ አገሮች መንግስታት መሀከል ያለው ችግር ይህንን የፖለቲካ ኢኮኖሚክስ ህግ ለመረዳት ያለመቻል ነው።
የፖለቲካ ኢኮኖሚክስን ህግ እስካልተረዳን ድረስ ደግሞ የውጭ ኃይሎች እየመጡ እንደፈለጉ ያሽከረክሩናል።

ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት በምናወራበት ጊዜ የኢኮኖሚ ዕድገትን እንደ ዐላማ አድርገን መውሰድ የለብንም። ማንኛውም ህብረተሰብ ለኢኮኖሚ ዕድገት ብሎ አይደለም

የሚኖረው። ለመኖር ሲል ግን ማንኛውም ህብረተሰብ በኢኮኖሚና በማንኛውም እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ አለበት። ስራ የሰውን ምንነት መግለጪያ እንደመሆኑ መጠን፣ የሰው ልጅ ሲሰራ ብቻ ነው በዚህች ዓለም ላይ ሊኖር የሚችለው። ስለዚህም በሳይንስ የተደገፈ የኢኮኖሚ ዕድገት አንድን ህብረተሰብ እንደ ህብረተሰብ እንዲኖርና ታሪክ ሰርቶ
ለሚቀጥለው ትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ መሰረታዊ መመሪያ መሆን አለበት። ስለዚህም የኢኮኖሚ ዕድገት ከሌሎች መሰረታዊ ጉዳዮች ተነጥሎ በፍጹም ሊታይ የሚችል አይደለም። አንድ ቦታ ላይ እንዳልኩት፣ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና ዕድገት በቦታ የሚወሰን ነው። የቦታን አደረጃጀት ይፈልጋል። በሌላ አነጋገር፣ ከላከተማ ዕድገት፣ ከአገራችን የአየር ጠባይ ጋር ሊሄድ የሚችል የቤት አሰራርና የገበያ አዳራሽ ሳይኖር ስለ ገበያ ኢኮኖሚም ሆነ ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት ማውራት አይቻልም። ዛሬ በአገራችንና በሌሎች
የአፍሪቃ አገሮች የሚታየው የተዘበራረቀና ዕቅድ የሌለው የህንጻ አሰራር ረጋ ላለ የገበያ ኢኮኖሚ ዕድገት የሚያመች አይደለም። ከተፈጥሮ ህግ፣ በተለይም ደግሞ ከዩኑቨርስ አንጻር የተነደፈ አይደለም። ለጥቂቶች መፈንጫ ተብሎ የሚሰራ የህንጻ ስራ ነው የሚካሄደው።

ስለዚህ ወደ ፊት በሰፊው በዚህና በሌሎች መሰረታዊ ነገሮች ላይ ብንወያይ አማራጭ መፍትሄ ማቅረብ እንችላለን። ከአንዳንድ ድህረ-ገጾች እንደምመለከተው ብዙ ወርቅ ወርቅ አስታሳሰብና ሰፊ አድማስ ያላቸው ኢትዮጵያውያን እንዳሉ መገንዘብ ይቻላል። እነዚህ የምሁር ኃይሎች ከፖለቲካ ስልጣን ባሻገር ምሁራዊ ኃይል ወደ መሆን ማምራት አለባቸው። በጥቃቅን ነገሮች መወጠር የለባቸውም። ጊዜው ትንሽ ረዘም ቢልም ቆንጆ ኢትዮጵያን የመመስረቱና የመገንባቱ ጉዳይ የማይቀር ነው። ስለዚህ ወደዚያ ለማምራት ጠንክረንና ተባብረን መስራት አለብን።
**ፈቃዱ በቀለ**

ማሳሰቢያ: ለውይይት እንዲያመቸን ምናልባት እነዚህን መጽሀፍቶች ለማታውቁ ብትመለከቷቸው ጥሩ ይመስለኛል።

- Brett, E.A; International Money and Capitalist Crisis: The Anatomy of Global
Disintegration, London 1983
- Bowler J.Peter; The Environmental Science, London &New York, 1992
- Cowley, Catherine; The Value of Money: Ethics and the World of Finance, London &
New York 2006
- Meštrović Stjepan; The Barbarian Temprament: Toward a Postmodern Critical Theory,
London, 1993
- Seung, T.K; Plato Rediscovered: Human Value and Social Order, London 1996__